

# ቤዛ

ከሥርጉተ ሥላሴ

ሰው ሰውነቱ፡ ሰው እሱነቱ፡ ሰው ማንነቱ ... የሚገለጠው በውስጡ በአሰረጸው የብቃት መክሊት ነው። ውስጡን ውስጥ የሚያደረገው ደግሞ ተግባሩ ነው። ተግባሩ እሱነቱን፣ ማንነቱን፣ ሰውነቱን ፍንትው አድርጎ ያሳያል።

***የሰው ሰውነቱ መግለጫው ዓውራው ድርጊቱ ነው። ድርጊት የራስነት መግለጫነቱን የሚያሳየው ደግሞ የግል ጥቅምን ድጦ ወይንም ጨፍልቆ ለህዝበ ጠቀም ተግባር ዋቢ መሆን ሲችል ብቻ ይሆናል። ረቂቁ የህሊና ውሳኔ ከድርጊት ጋር ሲዋሀድ  ቅኔ ይሆናል። ቅኔው ደገሞ ቤዛ ይሆናል።***

እንግዲህ ይህን የነጠረ ቤዛነት በድርጊት ተጸንሶ ተወልዶ አድጎ እና ጎልምሶ በማሳየት እረገድ ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር ዋቤያችን ናቸው።

ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ ተፈጥሮአቸው በራሱ ፍቅርን የመሸመት በፍቅር የማናችንንም ህሊና የመቆጣጠር ብቃቱን መለካት አይቻልም። በእኔ ደርሶ አይቸዋለሁ እና። ይህን በስማ በለው ሰምቼ ሳይሆን በዓይኔ ያየሁት የጨበጥኩት የዳሰስኩት ሀቅ ነው።

ክብርትነታቸውን የሚወዱ ሰዎች ከልባቸው ነው የሚወዷቸው። ከሃቅ ጋር የተጋቡ ሰዎች ሁሉ በልባቸው ሙዳይ ውስጥ ውስጣቸውን ውስጥ አድረገውታል። ሁሉንም በማቻቻቻል በትህትና እና በትዕግስት የማስተናገድ ብቃታቸው በአህድዮሽ እውነት ፈላጊ ወገኖቻቸውን ሁሉ በ80 አጋብቶናል። ሃቅ ነው አይደል? መስክሩ!!!

ቀለበታችን፣ ውላችን፣ ኪዳናችን፣ ሚዛናችን፣ ፅናታችን፣ ቤዛችን ናቸው። ቤዛ ክቡር ለሆነው የነጠረ ፍቅር የሚሰጥ የኪዳን መሰዋያ ነው።

የቃል አርበኛዋ የቃል አብዮተኛዋ የአጤ ቴዎድሮስን፣ የብዕፁ አባታችን የሰማዕቱን አቡነ ጴጥሮስ ቤዛነት በድርጊት ለዘመኑ መገቡት። በድርጊት የሴቶችን የተጋድሎ ብቃተ መክሊት አስጌጡት። **ትውፊትን ተረክበው ትውፊትን ፈጠሩት።**

እግዚአብሔር አምላክ ለዓይነ  ሥጋ ያብቃን።
አሜን!
እንጽና!